## *የ1999 የግብርና ናሙና ጥናት*
## *የተቆጣጣሪዎች መመሪያ*

**1.*መግቢያ***

*የኢትዮጵያ ሕዝብ በአብዛኛው በግብርና ዘርፍ ላይ የተሰማራ ሲሆን ይህም የአገር ውስጥን አጠቃላይ ምርትና የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ከፍተኛ ድርሻ የያዘ ክፍለ ኢኮኖሚ ነው:: ከዚህ በመነሳት የሕዝቡን የአመጋገብ ሁኔታና የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የግብርና ምርት ጥራትንና የምግብና የእርሻ ውጤቶችን ሥርጭት እንዲሁም በግብርና ላይ የተሰማራውን ሕዝብ አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል በየጊዜው ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል::*

*ስለዚህ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ አወቃቀርና ሌሎች የግብርና ባሕሪያትን በሚመለከት አስተማማኝ የሆነ ስታቲስቲካዊ መረጃ መኖር አስፈላጊ በመሆኑ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ላለፉት ዓመታት በናሙና በተመረጡ ገበሬ ማህበራት/ ቆጠራ ቦታዎች / ላይ በማተኮር የግብርና መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች ሲያቀርብ መቆየቱ ይታወሳል:: ይህም የአገሪቱን የዕድገት ፕላን ቅደም ተከተል ለማመቻቸት ከሞላ ጎደል በመንደርደሪያነት ሲያገለግል ቆይቷል:: ሆኖም ይህ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ በስፋትና በጥልቀት የሚያሳይ ስታቲስቲካዊ መረጃ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት 1999 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት ይካሄዳል::*

### **1.1 *የእርሻ ሰብል ትንበያ ዓላማዎች***

*በ1999 ዓ.ም ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ የሀገሪቱን ክልሎች በሙሉ የሚሸፍኑና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የሚካሄደው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው::*

1. *የዚህ ጥናት መሠረታዊ ዓላማ በ1999 ዓ.ም ሰብል ዘመን ሊገኝ የሚችለውን ምርት በመገምገም በምርት ዘመኑ ሊመረት የሚችለውን ጠቅላላ የምርት መጠን (**Total production forecast**) ከወዲሁ መገመትና ወደፊት በሀገሪቱ ሊመረት የሚችለውን የምርት መጠን መተንበይ እንዲሁም፤*

2. በ1999 ዓ.ም የምርት ዘመን ትርፍ ምርት ሊያመርቱ የሚችሉትንና የምርትእጥረት ሊደርስ የሚችልባቸውን ክልሎች መለየት የሚያስችሉ የትንበያ መረጃዎችን ማቅረብ ናቸው፡፡

**1.2. <u>የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች</u>**

በሰብል ትንበያ ጥናት የሚገኙ የትንበያ መረጃዎች ከሚሰጡት በዛ ያሉ ጥቅሞች መሀል በተለይ መንግሥት ለሚነድፋቸው አዳዲስ ፖሊሲዎችና የረዥምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች ከሚሰጡት ጥቅም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. በሀገር ውስጥ ለምግብ ፍጆታ የሚውል ሰብል በቂ ወይም አነስተኛ መሆኑን በቅድሚያ መገመት በሰብል ምርት ወደፊት በሀገሪቱ ሊደርስ የሚችለውን እጥረት ወይም ትርፍ ለመገምገም ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ከሀገር ውስጥ ወደ ውጭ ለመላክ ( Import-Export ) ወቅታዊ እርምጃዎች ለመውሰድ ፣ መንግሥት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርግ የወደፊቱን በቅድሚያ በማሳወቅ የትንበያ መረጃ ትልቁን ሚና ይጫወታል፡፡

ለ. የትንበያ መረጃዎች በምርት ዘመኑ በሀገሪቱ ትርፍ ምርት ሊያመርቱ የሚችሉ ክልሎችን በመጠቀም በክልሎቹ በሚገኘው ትርፍ ምርት ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ የተለያዩ ችግሮችን ለምሣሌ በሰብል ማከማቻ ችግር ምክንያት የምርት ብክነት እንዳይኖር ጊዜያዊ ማከማቻዎችን ለመሥራት እንዲሁም ትርፍ ምርት በመኖሩ ምክንያት ሊደርስ በሚችለው የሰብል ዋጋ መውደቅ ገበሬው እንዳይጎዳ መንግሥት ሊወስድ የሚገባውን እርምጃ በቅድሚያ መንደፍ፡፡

ሐ. በአንጻሩ የምርት እጥረት ሊደርስባቸው የሚችሉ ክልሎችን በመጠቀምመንግስት በክልሎቹ ሊደርስ የሚችለውን የሰብል ምርት እጥረት ከወዲሁ በመረዳት እጥረቱ ሊወገድ የሚችልበትን መንገድ ለመተለም ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያመቻች በማስጠንቀቅ ወደፊት ሊገጥም የሚችለውን ችግር ለማስወገድ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለመንደፍ . . . ወዘተ ይጠቅማሉ፡፡

## 1.3 <u>የግብርና ናሙና ጥናት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች</u>

የግብርና ናሙና ጥናት የሚከተሉትን ዋና ዋና ጥቅሞች ያስገኛል፡፡

### ሀ. <u>ለፕላን ዝግጅት ፣ ለፖሊሲና አስተዳደራዊ ውሣኔዎች ያገለግላል፡፡</u>

ስለግብርና አጠቃላይ ባህሪ ማወቅ በወቅቱ ያለውን የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የእድገት ደረጃና ችግሮች ለመገምገምና ይህንኑ መሠረት በማድረግ በግብርና የተሰማራውን ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ይበልጥ ለማሻሻል የሚያስችሉ አግባብ ያላቸውን ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች ለመንደፍ ያስችላል፡፡ በተለያዩ የአስተዳደር ክፍሎች የሚኖረውን በግብርና የተሰማራ ሕዝብ ብዛት ከማሳወቁም በላይ እያንዳንዱ የአስተዳደር ክልል በተለይ የተሰማራበትን የግብርና ዓይነት ወይም ሁኔታ ለማወቅ ስለሚቻል የተመጣጠነና ሚዛናዊ የሆነ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ረገድ ታላቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

### ለ. <u>ለንግድና ለእንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ታላቅ አገልግሎት ይሰጣል</u>

የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ከንግድና ኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር በጣም የጠበቀና የተቀራረበ ግንኙነት ስላለው በንግዱ ዘርፍ የግብርና ውጤቶችን ፍላጎትና አቅርቦት ለማወቅና በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ለሚደረጉ ግብይቶች በቅድሚያ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ይረዳል፡፡ እንዲሁም የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ አስመልክቶ የግብርና ውጤቶች ለኢንዱስትሪው ፣የኢንዱስትሪው ውጤቶች ደግሞ ለግብርናው የሚሰጡት ጠቀሜታ ተጣጥመው እንዲገኙ ለማድረግ ጥናቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

### ሐ. <u>በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የተደረጉትን ለውጦች ለመገምገም መሠረት ይጥላል</u>

በተለያዩ የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በተወሰዱ ፖሊሲዎችና እርምጃዎች ምክንያት የተደረሰባቸውን ለውጦች ለመገምገም እንዲቻል መነሻ መኖር ይኖርበታል፡፡ የለውጡን ይዘት ለማጤን መሠረታዊ መረጃ በቅድሚያ ማጠናከሩ ሁኔታዎችን ለማወዳደርና ለማነጻጸር ያገለግላል፡፡ በዚህም በኩል ጥናቱ መሠረታዊ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ስለሚያደርግና ይህም ተጠናክሮ መገኘት የሁኔታዎችን ለውጥ ለመገምገም ዓይነተኛ መሠረት በመሆን ያገለግላል፡፡

መ. <u>የምርምርን ተግባር ያፋጥናል</u>

የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ባህርያትን አስመልክቶ ሰፋትና ጥልቀት ያለው ምርምር ለማካሄድ የሚረዱ አንዳንድ መረጃዎች ከጥናቱ ስለሚገኙ በዚሁ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

## 2. <u>የግብርና ናሙና ጥናት የተቆጣጣሪዎች አጠቃላይ መመሪያ</u>

እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ለመስክ ሥራ ብቁና ታታሪ መሆን ይገባዋል፡፡ እንዲሁም በተመደበበት ቦታ በሥሩ የተመደቡትን መረጃ ሰብሳቢዎች በማስተባበር፣ በመቆጣጠር፣በመከታተልና በመርዳት መረጃዎቹ በትክክል እንዲሰበሰቡ የማድረግ ኃላፊነት ስላለበት ይህንን ለመወጣት የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል ይኖርበታል፡፡

### 2.1 <u>የተቆጣጣሪው ሚና</u>

በ1999 ዓ.ም የሚካሄደው የግብርና ናሙና ጥናት የዋናው የመኸር ወቅትና የበልግ ወቅትን የግብርና ሁኔታ ያጠቃልላል፡፡ መረጃዎቹም በገጠር ከግል ባለይዞታዎች በተጨባጭ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና በቃለ መጠይቅ ይሰበሰባሉ፡፡ የመስክ ተቆጣጣሪ ጥናቱን የሚያስፈጽመውን ክፍልና መረጃ ሰብሳቢዎችን የሚያገናኝ ድልድይ እንደመሆኑ መጠን በመስክ በመገኘት ሥራ ይመድባል፣ አስፈላጊ የሆኑ የቆጠራ ካርታና የመስክ መገልገያ ያከፋፍላል፣የተጠናቀቁ ቅጾችን በመሰብሰብ በመመሪያው መሠረት በትክክል መሞላቱን ያረጋግጣል ወቅቶችን በመጠበቅ ወደ ቅ/ጽ/ቤት ይልካል፡፡ ተቆጣጣሪው ወቅታዊ የሆነ ተጨማሪ መመሪያ ካለ ያስተላልፋል፣አስፈላጊም ከሆነ መረጃ ሰብሳቢውን በሥራ ያግዛል፡፡

በመስክ ላይ ሊመለሱ ያልቻሉና መፍትሄ ያልተገኘላቸው ጥያቄዎችን በመሰብሰብ ሥራው ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች በማቅረብ የተሰጠውን መፍትሄ በሥራ እንዲተረጎም ያደርጋል፡፡

ለመረጃ ሰብሳቢዎች የቃለ መጠይቅና የተጨባጭ መረጃ አሰባሰብ ዘዴን አስመልክቶ ሰፋ ያለ ሥልጠና ይሰጣል፡፡ ይህም ሥልጠና መረጃ ሰብሳቢዎች የማይራራቅ ዕውቀት እንዲኖራቸው እንደሚያደርግ ቢታመንም የያንዳንዱን መረጃ ሰብሳቢ የተፈጥሮ ባህርይ ከቃለ መጠይቁ የሚገኘውን መረጃ ሊያለያየው ይችላል፡፡ ስለዚህ በቃለ መጠይቁ ባለይዞታውን እንዴት መቅረብ እንዳለበትና ምን ዓይነት መረጃ በምን ዓይነት ዘዴ ሊያገኝ እንደሚችል ጠንቅቆ

ማወቅ የመረጃ ሰብሳቢው የሥራ ድርሻ ስለሆነ ይህንን ለማሟላት ቅጾችንና የአሞላል መመሪያዎችን ከወዲሁ በደንብ መረዳትና ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ከመስክ ተቆጣጣሪም ግንባር ቀደም ተግባሮች አንዱ መረጃ ሰብሳቢውን በቴክኒክ በኩል መቆጣጠር ስለሆነ እንደ መረጃ ሰብሳቢው ቅጾቹንም ሆነ የአሞላል መመሪያውን በደንብ ማወቅ ይገባዋል፡፡

ተቆጣጣሪው ኃላፊው በሚሰጠው የቆጠራ ቦታዎች ዝርዝር ውስጥ የተመደቡትን መረጃ ሰብሳቢዎች ሥራ በየጊዜው በቅርብ መቆጣጠር አለበት፡፡ የግብርና ናሙና ጥናቱ ሥራ ለግል ባለይዞታ የሚከናወነው በተመረጡት የቆጠራ ቦታዎች በተመረጡት ባለይዞታዎችና ማሣዎች ላይ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የሚሰበሰበውን መረጃ ጥራት ለማጠናከር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች ወይም ኤክስፐርቶች በየወቅቱ የመስክ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡

## 2.2 <u>ሥልጠና</u>

የመስክ ተቆጣጣሪዎችም ሆኑ መረጃ ሰብሳቢዎች ሥልጠና ለጥናቱ ሥራ አስፈላጊነቱ የታመነ ቢሆንም በተለይ ተቆጣጣሪዎች ካላቸው የሥራ ድርሻ አንጻር የመረጃ ሰብሳቢዎችን ሥልጠና ሙሉ በሙሉ መካፈል አለባቸው፡፡ ይህም የቃለ መጠይቁን አቀራረብ ሁኔታና ፣የማሳዎችን ልኪ ሁኔታ እንዲሁም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ቅጾችን በሙሉ የሚያጠቃልል ሲሆን ተቆጣጣሪው ወደፊት ለሚገጥመው ቴክኒካዊ የቁጥጥር ሥራ ከፍተኛ እገዛ ያደርግለታል፡፡

## 3. <u>የመስክ ተቆጣጣሪ መሠረታዊ ተግባሮች</u>

የመስክ ሥራውን ተግባራዊ በማድረግ በኩል አንድ ተቆጣጣሪ የሚያከናውናቸው ተግባራት በሁለት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡

- የሥራ አፈጻጸሞችን መቆጣጠርና አስተዳደራዊ ሥራዎችን ማከናወን፣
- ቴክኒካዊ የመስክ ቁጥጥር ማድረግ፡፡

## 3.1 <u>የሥራ አፈጻጸሞችን መቆጣጠርና አስተዳደራዊ ሥራዎችን ማከናወን</u>

መመሪያዎችንና የመስክ ሥራ መዋቅሩን ተግባራዊ ለማድረግ የሥራ አፈጻጸሞችን በመቆጣጠርና አስተዳደራዊ ሥራዎችን በማከናወን በኩል ከዚህ የሚከተሉት የተቆጣጣሪዎች ኃላፊነት ይሆናሉ፡፡

ሀ. ከኃላፊው ጋር በየጊዜው ግንኙነት በማድረግ ፣ በጊዜው በተቆጣጣሪው ያልተፈቱ ችግሮችን ከመረጃ ሰብሳቢው ተቀብሎ ወደ ላይ በማስተላለፍ በወቅቱ መፍትሄ ማስገኘት፣

ለ. ከሥምሪቱ በፊት ለመቆጣጠሪያ ክልሉ በቂ የሆኑ የመስክ ቁሳቁሶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ወይም በሥሩ ላሉት መረጃ ሰብሳቢዎች በቂ መጠይቆች ፣ የጽህፈት መሣሪያዎች ፣ ኮምፓስ፣ሚዛን፣ገመድ፣. . . ወዘተ እንዲሁም ለቁጥጥሩ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በቂ መሆናቸውን ማረጋገጥ ካልተሟላ እንዲሟላ ማድረግ በተጨማሪም እያንዳንዱ መረጃ ሰብሳቢ የሚመደብበትን ቆጠራ ቦታ አስመልክቶ አስፈላጊውን ሁሉ ይኸውም ቆጠራ ቦታው ምን ያህል ባለይዞታዎች ወይም ቤተሰቦች እንዳሉት፣ የግብርናውን ሁኔታ፣የቆጠራ ቦታውን የመልክዓ ምደራዊ አቀማመጥ፣የመጓጓዣ ሁኔታና መጠለያን በሚመለከት አስቀድሞ ማወቅ፣የመስክ ሥራውን የሚመለከት ቁጥጥር እንዴት እንደሚደረግ ለምሣሌ እንደገና ቃለ መጠይቅ ወይም ማሣ ልኪቶሽ መቼ ማድረግ እንደሚገባ እቅድ ማውጣት ይገባል። እነዚህና የመሳሰሉትም ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ ለማዘጋጀት ወይም ለመወሰን የሚረዱ ይሆናሉ።

ሐ. በተመረጡ ቆጠራ ቦታዎች በመገኘት የመጓጓዣ ሁኔታዎችን፣ከከተማ ርቀታቸውንና ለመረጃ ሰብሳቢው የተዘጋጀውን መጠለያ በማየት ችግር ካለ ማቃለል ከአቅም በላይ የሆነውን በወቅቱ ሪፖርት ማስተላለፍ ይህም ለቆጠራ ቦታው የሚያስፈልገውን የመጓጓዣ ዓይነት ለመወሰን መሻሻል የሚያስፈልገውን መጠለያ ለማሻሻል ወይም ለማስተካከል ይረዳል።

መ. ከአካባቢና የቆጠራ ቦታው ከሚገኝበት ገበሬ ማህበር ባለሥልጣኖች ጋር ቀደም ብሎ በመገናኘት ስለጥናቱ ዓላማና ጥቅም በማስረዳት ድጋፍ ማግኘት የሚሰበሰበውን መረጃ ሚስጢራዊነት ማሳወቅና ለተቆጣጣሪውም ሆነ ለመረጃ ሰብሳቢው ሥራውን በሚመለከት አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግ መጣር ሁኔታው ካልተሳካ ወይም ከአቅም በላይ ከሆነ ደግሞ ለኃላፊው በወቅቱ ማሳወቅ።

ሠ. ተቆጣጣሪው በሥሩ ያለውን እያንዳንዱን መረጃ ሰብሳቢ አስመልክቶ ስለተመደበበት ቆጠራ ቦታ ሁኔታ ከስምሪቱ በፊት በዝርዝር ማለትም ከላይ ከሀ - መ ተቆጣጣሪው ቀደም ብሎ ያጣራቸውንና መፍትሄ የሰጣቸውን ሁኔታዎች በሙሉ ማስረዳት ይህም መረጃ ሰብሳቢው ስለሁኔታው ቀደም ብሎ ዝግጅት ወይም ጥንቃቄ እንዲያደርግ ከመርዳቱም በላይ በግል የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ለማሟላት በቂ ጊዜ ይሰጠዋል።

ረ. ከመስክ ሥራው ፍጻሜ በኋላ የተሞሉ መረጃዎችን በሙሉ በመሰብሰብና በመመሪያው መሠረት መሞላታቸውን በማረጋገጥ ለሚመለከተው ክፍል ማስረከብ ወይም መላክና በጥንቃቄ መድረሳቸውን ማረጋገጥ፣

ሰ. ሌሎች አስተዳደራዊ ሥራዎችን መሥራት፣ ይህም ለተቆጣጣሪው በኃላፊው በኩል የሚደርሱትን አስተዳደራዊ ሥራዎች በሙሉ ሲሆን ለምሣሌ የመረጃ ሰብሳቢን ወይም ሌላ የመስክ ሠራተኞችን ደመወዝ በወቅቱ መክፈል፣ሌሎች ጥናቱን የሚመለከቱ ክፍያዎችን መፈጸምና አፈጻጸማቸውን የሚያመለክት ማስረጃ ለሚመለከተው ክፍል በወቅቱ ማድረስ፣ጥናቱን የሚመለከቱ መረጃዎችንና አስተያየቶችን ከተለያዩ ምንጮች መሰብሰብና ሪፖርት ማድረግ፣. . . ወዘተ

## 3.2 <u>የተቆጣጣሪን ቴክኒካዊ የመስክ ቁጥጥር ማድረግ በሚመለከት የሚከናወኑ ተግባራት፡፡</u>

ሀ. በጥናቱ ወቅት የጊዜ ሠንጠረዥ በማውጣት መረጃ ሰብሳቢዎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ፣

ለ. የቆጠራ ቦታው ድንበሮች በቆጠራ ካርታው የተመለከቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ. የተጠናቀቁ መጠይቆችን አንድ በአንድ በመመርመር በመመሪያው መሠረት መሞላታቸውን ማረጋገጥ መታረም የሚገባቸውን ደግሞ እንዲታረሙ ማድረግ፣

መ. በመረጃ ሰጪዎች ወይም በሌላ ችግር ምክንያት ያልተጠናቀቁ ወይም መልስ ያልተሰጠባቸውን መጠይቆች በሚመለከት በቦታው በመገኘት ችግሩ እንዲቃለል ማድረግ፣

ሠ. ጥናቱ በሚካሄድበት ቦታ በመገኘት መረጃ ሰብሳቢው የሚሰራው በተመረጠ ቤተሰብ ወይም ባለይዞታ ወይም ማሣ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ. ለጥናቱ ከተመረጡት ቤተሰቦች ውስጥ በተወሰኑ ማሳዎች ላይ የእንደገና ማሣ ልኪቶሽ ማከናወን እንዲሁም የተወሰኑ ባለይዞታዎችን እንደገና ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣

ሰ. እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ጉብኝቱን አስመልክቶ ለኃላፊው ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

ሸ. እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ለቁጥጥር ከመሰማራቱ በፊት ስለሚያከናውነው ሥራ ከኃላፊው ጋር ውይይት ወይም ምክክር ማድረግ አለበት፡፡

ቀ. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ቴክኒካዊ ሥራዎችን ይሠራል፡፡

## 4. መጠይቆችን ስለመመርመር

### 4.1 አጠቃላይ መመሪያ

በእያንዳንዱ የመስክ ጉብኝት የተጠናቀቁ መጠይቆችን አንድ በአንድ ወዲያውኑ በመመርመር በመመሪያው መሠረት መሞላቱን ማረጋገጥ የተቆጣጣሪው ኃላፊነት ነው፡፡

የተቆጣጣሪውን ሥራ ለመለየት ያስችል ዘንድ እርማት ካለ መደረግ ያለበት መረጃ ሰብሳቢው ከሚጠቀምበት ቀለም ዓይነት የተለየ መሆን አለበት፡፡ የማያጠራጥሩና ግልጽ የሆኑ ስህተቶች ከተገኙ ተቆጣጣሪው እዚያው ማረም አለበት፡፡ ሆኖም መረጃውን ለማስተካከል የባለይዞታው ወይም የማሣዎች ጉብኝት የሚያስፈልገው ከሆነ መረጃ ሰብሳቢው ቦታው ድረስ በመገኘት እንዲያስተካክል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ ተቆጣጣሪው የተጠናቀቁ ቅጾችን በሚገባ ለመመርመር የሚችለው አሞላላቸውን በቀጥታ በማየት፣የእንደገና ቃለ መጠይቅና የእንደገና ማሣ ልኪቶሽ በማድረግ ይሆናል፡፡

### 4.2 የመጠይቆችን አሞላል ስለመመርመር ዝርዝር መመሪያ

በ1999 በሚካሄደው የግብርና ናሙና ጥናት በመስክ ቁጥጥር መጠይቆችን እንዴት መመርመር እንደሚቻል ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል፡፡

በጥናቱ የሚሸፈነውን የቆጠራ ቦታ አስመልክቶ የአካባቢ መለያው የክልል፣የዞን፣የወረዳ፣የገበሬ ማህበሩና የቆጠራ ቦታ ስም ወይም ቁጥር የባለይዞታው ስም፣ዕድሜ፣ጾታና የግብርናው ዓይነት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ መመዝገቡን ማረጋገጥ፡፡

<u>ቅጽ ግ.ና.ጥ ስ.ት.ጥ 99/3ሀ 99/3ለ 99/3ሐ እና 99/3መ</u>

<u>የሰብል ሁኔታ ግምገማ</u>

በዚህ ቅጽ ለትንበያ የሚያገለግሉ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ስለሆነ በመመሪያው መሠረት መሞላቱን ማረጋገጥ፣የሚያጠራጥሩ መረጃዎች ከተገኙ ባለይዞታውን ማነጋገርና ማሳዎችን መጎብኘት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ዓምዶች መገናዘብ እንዳለባቸው ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ በቅጽ 99/3ሀ በክፍል 2 በዓምድ 6 ኮድ 1 ከተሞላ በዓምድ 7 የሚጨምረው ምርት መጠን በመቶኛ መሞላት እንዳለበት፣በዚሁ ክፍል

ዓምድ 6 ኮድ 3 ከተሞላ በዓምድ 9 የሚቀንሰው መጠን በሙቶኛ ተሞልቶ ለመቀነስ ዋነኛ ምክንያት የሆነው በዓምድ 10 መገለጽ እንዳለበት መገንዘብ ያስፍልጋል:: ሌሎችንም ዓምዶች በመመልከትና ቁጥጥር ማድረግ ሊከሰቱ የሚችሉበትን ስህተቶችን መቀነስ ይቻላል::

## <u>ቅጽ ግ.ና.ጥ 99/2ሀ- በጊዜያዊ /በድብልቅ/ በቋሚ ሰብሎች (አትክልትና ሥራሥር ተክሎችን ጨምሮ) የተያዙ ማሳዎች/ሌላ መሬት አጠቃቀም ዝርዝር ሁኔታ እና የስፋት ልኪ ውጤት /በመኸር ወቅት/</u>

ይህ ቅጽ በመኸር ወቅት ለጥናቱ በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ለሚገኙ የግብርና ባለይዞታዎች በሙሉ ይሞላል:: በክልሉ ጥናቱ የተካሄደበት የአካባቢ መለያ በትክክል መሞላቱ ከተረጋገጠ በኂላ ክፍል ሁለት ማሣዎች/ሌላ የመሬት አጠቃቀም የሚዘረዘሩበት እና ክፍል ሦስት የስፋት ልኪ ውጤት የሚመዘገብበት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ይህ ቅጽ ባለይዞታው ያሉት ጠቅላላ በጊዜያዊ /በድብልቅ/በቋሚ ሰብል የተያዙ ማሳዎች እንዲሁም ሌላ የመሬት አጠቃቀም የሚመዘገቡበት እና የማሳ ስፋት ልኪ ውጤት የሚሞላበት ሲሆን በእያንዳንዱ ማሣ ላይ ያለው የሰብል ዓይነት/መሬት አጠቃቀም የፓርሰልና የማሣ ቁጥር አሰጣጥ የፓርስልና የማሳ ቁጥር ትርጉምን በተከተለ መልኩ ተገናዝቦ በክፍል 2 በዓምድ 17 መሞላቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ለእያንዳንዱ የተመዘገበ ሰብል/ሌላ መሬት አጠቃቀም በክፍል 2 ዓምድ 16 የቀረቡት ጥያቄዎች ተጠይቀው በዓምድ 17 መልሶች መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በክፍል 3 ከዓምድ 19-26 ደግሞ የስፋት ልኪ ውጤት ( ለእያንዳንዱ የማሳ/ሌላ የመሬት አጠቃቀም ጎን በኮምፓስ ተለክቶ የተገኘ ቤሪንግ ፣ርዝመት በሜትር እንዲሁም ስፋት በስኬር ሜትርና ከ5% በታች የሆነ Closure error ተሰጡት ክፍት ቦታዎች ተሟልተው መሞላታቸውን ተጣጣሪው ማረጋገጥ አለበት:: አንዱ ቅጽ በፊት ለፊት በኩል ለአንድ ማሳ/መሬት አጠቃቀም በስተጀርባ በኩል ደግሞ ለሌላ ማሳ/መሬት አጠቃቀም መመዝገቢያ የሚያገለግል ነው::

## ቅጽ ግ.ና.ጥ 99/2ለ

ይህ ቅጽ አጠቃላይ ይዞታን የሚሞከቱ መረጃዎች (በባለይዞታ ደረጃ) የሚሞላበት ነው:: በዚህ ቅጽ በዓምድ 16 አጠቃላይ ይዞታን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: በዚሁ ዓምድ የቀረቡት አጠቃላይ ጥያቄዎች በባለይዞታ ደረጃ መጠየቃቸውንና ለተገኙትም መልሶች ትክክለኛ ኮዶች በጥያቄዎቹ ትይዩ በዓምድ 17 በተሰጡት ክፍት ቦታዎች መሞላታቸውን ተቆጣጣሪው ማረጋገጥ አለበት::

## የቅጽ ግ.ና.ጥ. 99/4ሀ የመኸር ወቅት ምርት ጥናት የሰብል ሁኔታ ግምገማ

በ1999 ዓ.ም. ግብርና ናሙና ጥናት የሰብል አጨዳ እንደማይካሄድ በመረጃ አሰባሰብ መመሪያው ላይ ተገልጾአል:: ነገር ግን በዋናው መኸር ወቅት ሊመረት የሚችለውን ወይም የተመረተውን ምርት መጠን ለማወቅ ያስችል ዘንድ ይህ ቅጽ ማለትም ቅጽ 99/4ሀ ተዘጋጅቷል የቅጹም ይዘት ከሰብል ትንበያ ቅጽ ሰ.ት.ጥ. 99/3ሀ ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ በመሆኑ ለዚሁ ቅጽ የተሰጠውን መመሪያ በመከተል መረጃው መሰብሰቡን ተቆጣጣሪው ማረጋገጥ አለበት::

## የቅጽ ግ.ና.ጥ 99/4ለ፣ቅጽ ግ.ና.ጥ 99/4ሐ እና ቅጽ ግ.ና.ጥ 99/4መ የመኸር ወቅት ምርት ጥናት የሰብል ሁኔታ ግምገማ

እነዚህ ቅጾች በመኸር ወቅት የምርት ጥናት የሰብል ሁኔታ ግመገማ ለማካሄድ ሚያገለግሉ ናቸው:: በነዚህ ቅጾች የሚሰበሰቡት መረጃዎች በሰብል ትንበያ ወቅት በቅጽ ሰ.ት.ጥ. 99/3ለ፣ ቅጽ ሰ.ት.ጥ. 99/3ሐ እና ቅጽ ሰ.ት.ጥ. 99/3መ ከተሞላው ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ሲሆኑ ያለው ልዩነት መረጃው የሚሰበሰብበት ወቅት ብቻ ነው:: ስለዚህ ይህ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ለሰብል ትንበያ የተሰጠውን መመሪያ የተከተለ መሆኑን ተቆጣጣሪው ማረጋገጥ አለበት::

## <u>ቅጽ ግ.ና.ጥ. 99/7- የቤት እንስሳት ፣ ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛትና የተዋፅዖ ምርት</u>

*ይህ ቅጽ የቤት እንስሳት ብዛትና የማር ምርት መጠን የሚሞላበት ሲሆን በክፍል ሁለት መጀመሪያ ላይ «አዎ» ለመለሱት መጠይቅ ይሞላል:: በጥያቄ 1 የዳልጋ ከብቶች ጠቅላላ ብዛታቸው ይሞላና ከነዚሁ ውስጥ የወንዶችና የሴቶች ብዛት ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው ይሞላል:: ከፊደል ሀ - ረ ለተዘረዘሩት የዳልጋ ከብቶች በየእድሜ ክልላቸውና አገልግሎታቸው አንጻር ጠቅላላ ብዛታቸውንና የወንድና የሴት ከብቶች ብዛት መሞላቱን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: በተመሳሳይ ጥያቄ 2፣3፣4፣5፣6፣7 ጠቅላላ ብዛታቸው ፣ የወንድና የሴት ብዛት እንዲሁም በየዕድሜያቸውና አገልግሎታቸው ለበጎች ፣ ለፍየሎች፣ለጋማ ከብቶች፣ለግመሎች መሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: በጥያቄ 8 ጠቅላላ የዶሮዎች ብዛት በአገልግሎት ዓይነትና በዝርያ ተለይተው መሞላታቸውንና ድምራቸው እኩል መሆኑንም ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: በጥያቄ 9 ንብ የያዙ ቀፎዎች በየዓይነታቸው ከተሞላ በኋላ በጥያቄ 10 ደግሞ የማር ምርት መጠን በኪ.ግ መሞላቱን ማረጋገጥ:: ጥያቄ 11 የወተት ላሞችና ግመሎችን የሚመለከት ሲሆን ከሀ-ሽ ያሉት ጥያቄዎች ተጠይቀው መሞላታቸውን እንዲሁም ጥያቄ 12 የእንቁላል ምርት (ብዛት) ጥያቄ 12 ደግሞ አማካኝ የእንቁላል መጣያ ወቅት በቀን በዝርያ ዓይነት መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንደዚሁም ጥያቄ 14 ባለፉት 12 ወራት የአንድ ዶሮ የእንቁላል አማካይ መጣያ ወቅት በዝርያ ዓይነት ተጠይቆ መሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: በጥያቄ 15 በዓምድ 2 ከተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ዓይነት በዓመቱ ውስጥ በበሽታ የተጠቁ ካሉ ብዛታቸው ጠቅላላና በጾታ ተለይቶ በዓምድ 3 እንደዚሁም በበሽታ ከተጠቁት ውስጥ ህክምና የተደረገላቸው ብዛት ጠቅላላና በፆታ ተለይቶ በዓምድ 5 መሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ጥያቄ 16 በዓምድ 2 ላይ የተዘረዘሩት የቤት እንስሳት ዓይነት በዓምድ 3 በጥናቱ ዓመት የተወለዱ ብዛት ፣ በዓምድ 4 የተገዙ ብዛት ፣ በዓምድ 5 በስጦታ ወይም በሌላ ምክንያት የተገኙ ብዛት ፣ በዓምድ 6 የተሸጡ ብዛት ፣ በዓምድ 7 የታረዱ ብዛት በዓምድ 8 የተሰጡ ብዛት በዓምድ 9 በበሽታ የሞቱና በዓምድ 10 በሌላ ምክንያት የሞቱ ብዛት ጠቅላላና በፆታ ተለይተው መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በጥያቄ 17 ዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የቤት እንስሳዎች በጥናቱ ዓመት ክትባት የተደረገላቸው ጠቅላላ ብዛት እንዲሁም በበሽታ ዓይነት በፆታ ተለይተው መመዝገባቸውንና*

ድምራቸው ከጠቅላላው ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ በጥያቄ 18 ዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የመኖ ዓይነቶች በዓምድ 3 መልሱ «አዎን» ከሆነ በዓምድ 4 ድርሻ በመቶኛ በዓምድ 5 ደግሞ የመኖው ምንጭ መሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ጥያቄ 19 በጥናቱ ዓመት ባለይዞታው በእንስሳት ኤክስቴንሽን ፓኬጅ መታቀፋቸው ተጠይቆ «አዎን» ከተሞላ በጥያቄ 20 የፓኬጁ ዓይነት መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## በስህተት መረጃ ሲመዘገብ የሚያመጣውን ችግር የሚያሳይ ምሣሌ

በአንድ ወረዳ ውስጥ በተመረጠ አንድ የቆጠራ ቦታ ውስጥ የሚገኝ መረጃ ሰብሳቢ በቆጠራ ቦታው ውስጥ በናሙና የተመረጡ የግብርና ይዞታ ያላቸውን ቤተሰቦች ጠቅላላ የቀንድ ከብቶች ብዛት ሲመዘግብ በአራት ቤተሰቦች ከዚህ እንደሚከተለው ስህተት ተፈጸመ እንበል ፣

| የባለይዞታ ተራ ቁ. | መመዝገብ የነበረበት | የተመዘገበው | የባለይዞታ ተራ ቁ. | መመዝገብ የነበረበት | የተመዘገበው |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 6 | 6 | 15 | 7 | 7 |
| 2 | 5 | 8 | 16 | 6 | 6 |
| 3 | 9 | 9 | 17 | 5 | 5 |
| 4 | 2 | 2 | 18 | 1 | 1 |
| 5 | 3 | 3 | 19 | 7 | 7 |
| 6 | 1 | 1 | 20 | 2 | 3 |
| 7 | 0 | 0 | 21 | 1 | 1 |
| 8 | 7 | 9 | 22 | 5 | 5 |
| 9 | 5 | 5 | 23 | 8 | 8 |
| 10 | 4 | 4 | 24 | 3 | 3 |
| 11 | 2 | 2 | 25 | 2 | 2 |
| 12 | 1 | 1 | 26 | 3 | 8 |
| 13 | 5 | 5 | 27 | 9 | 9 |
| 14 | 6 | 6 | 28 | 1 | 1 |
| | | | ድምር | 116 | 127 |

ከላይ እንደታየው የ2ኛ ፣ 8ኛ ፣ 20ኛ እና 26ኛ ባለይዞታዎች ቀንድ ከብት ቁጥር መረጃ ሲመዘገብ ስህተት በመፈጠሩ አጠቃላይ ድምሩ ላይ የ11 ለውጥ አስከትሏል፡፡ በመሆኑም ድምሩን ከ116 ወደ 127 ከፍ ያደርገዋል፡፡ ይህ ቁጥር በዚህ አንጻር ሲታይ ትንሽ ሊመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን በተመረጠው የቆጠራ ቦታ ውስጥ 160 የግብርና ቤተሰቦች ፣ 25 ናሙና ቤተሰቦች በወረዳው ውስጥ የተመረጠ 5 የቆጠራ ቦታዎች ቢኖሩ እንዲሁም የቆጠራ ቦታው የመመረጥ

እድል 0.00216 ቢሆን በተፈጠረው ስህተት የተነሳ በቆጠራ ቦታው ስሌቱ 619 መሆን ሲኖርበት ወደ 677 ከፍ ይላል:: የዚህ ልዩነት 58 ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ በወረዳ ደረጃ ሲሰላ ግምቱ 11457 መሆን ሲኖርበት ቁጥሩ ወደ 12534 ከፍ ይላል:: የዚህም ልዩነት 1086 ይናል ማት ነው:: እንግዲህ በተፈጠረው ስህተት ሳቢያ የሚመጣው ችግር ምን ያህል የገዘፈ እንደሆነ ከዚህ ምሳሌ መረዳት ይቻላል::

## 5. መልስ ያልተሰጠባቸውንና ተመሳሳይ ሁኔታዎችን በሚመለከት

### 5.1 «መልስ ያልተሰጠባቸው» ማለት ምን ማለት ነው?

እንደሚታወቀው ይህ ጥናት የሚከናወነው በናሙና አመራረጥ ላይ በመመስረት ነው:: እያንዳንዱ የተመረጠ ባለይዞታ /ማሣ ብዙ ያልተመረጡ ባለይዞታዎችን/ማሣዎችን የሚወክል መሆኑ ታውቆ ለተመረጠው ባለይዞታ/ማሣ የቃለ መጠይቁ/ተጨባጭ የመረጃ አሰባሰቡ በትክክል መካሄዱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለእያንዳንዱ የተመረጠ ባለይዞታም ሆነ ማሣ በቃለ መጠይቅ / በተጨባጭ ለጥናቱ የሚያስፈልገው መረጃ በሙሉ መሰብሰቡን ማረጋገጥ ለሥራው ጥራት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው:: መረጃ ሰብሳቢው ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሙት ይችላል:: መረጃ ሰብሳቢው በአንዳንድ የተመረጡ ባለይዞታዎች / ማሣዎች/ የሚፈለገውን መረጃ ሙሉ በሙሉ ለማግኘት ባለመቻሉ ሳይሞሉ የተተዉ ጥያቄዎች « መልስ ያልተሰጠባቸው » ይባላሉ:: ከመስክ ተቆጣጣሪው ዋና ዋና ተግባራት አንዱ ይህን ዓይነት መልስ ያልተሰጠባቸውን ምክንያቶች በተቻለ መጠን መቀነስ ይሆናል:: መልስ ያለማግኘት በብዙ ምክንያቶች ሊፈጠር ይችላል:: ነገር ግን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

1. መረጃ ሰብሳቢው የተመረጠውን ወይም ለቃለ መጠይቅ የሚፈለገውን ባለይዞታ መኖሪያ ቤቱ ማግኘት ያለመቻል፣
2. የተመረጠው ባለይዞታ ቃለ መጠይቅ እንዲደረግለት ያለመፈለግ ወይም ከተመረጠው ማሣ ላይ አስፈላጊው መረጃ እንዳይሰበሰብ መቃወም፣

### 5.2 መልስ ያልተሰጠባቸውን ጥያቄዎች በሚመለከት አጠቃላይ መመሪያ

ሀ/ መልስ ያልተሰጠባቸው ጥያቄዎች ብዙውን ጊዜ የሚፈጠሩት ከመረጃ ሰብሳቢው ድክመት ወይም ጥረት ያለማድረግ ነው:: ስለዚህ ይህንን በሚመለከት የመስክ ተቆጣጣሪው አስፈላጊ የሆነውን ቁጥጥር በማድረግ የመረጃ ሰብሳቢውን ሥራ መከታተል አለበት:: በመመሪያው መሠረት ለተመረጡት ባለይዞታዎች ቃለ

መጠይቅ መደረጉንና ለተመረጡት ማኣዎች አስፈላጊው መረጃ በመረጃ ሰብሳቢው መሰብሰቡን ተቆጣጣሪው ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለ/ በናሙና ያልተመረጠ ባለይዞታን ተመርጦ መረጃ ባልተሰበሰበበት/ መልስ ባልሰጠ ባለይዞታ መተካት ለችግሩ መፍትሄ ስለማይሆን በፍጹም መደረግ የለበትም፡፡ ስለዚህ ይህንን በጥብቅ መከታተል የመስክ ተቆጣጣሪው ኃላፊነት ይሆናል፡፡

ሐ/ « መልስ ያልተሰጠባቸውን » ጥያቄዎች ለመቀነስ ወይም እንዳይኖሩ ለማድረግ ዋናው መፍትሄ የተመረጠውን ባለይዞታ ለማግኘት በተቻለ መጠን ተደጋጋሚ ጉብኝት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ የተመረጠው ባለይዞታ እቤቱ የማይገኝ ከሆነ ቢያንስ ሶስት ቀጠሮ በመውሰድ ጉብኝት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ የመረጃ መሰብሰቡ ሥራ አልተሳካም ወደ ሚለው ውሳኔ ላይ መረጃ ሰብሳቢው ከመድረሱ በፊት ተደጋጋሚ ጉብኝት ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ተደጋጋሚ ጉብኝት ማለት የተመረጠውን ባለይዞታ ለማግኘት የሚደረግ ጉብኝት ነው፡፡ በተደጋጋሚ ጉብኝት ጊዜ የሚፈለገውን ሰው መቼና የት እንደሚገኝ አስቀድሞ ማወቁ በመስክ ሥራ ጊዜ በተደጋጋሚ ጉብኝት ያለአግባብ የሚባክን ጊዜን ያድናል፡፡

መ/ መልስ ስላልተሰጠባቸው ጥያቄዎች ማወቅ ለጥናቱ ስለሚረዳ / ለምሣሌ ፣ የባለይዞታው አለመገኘት ወይም መልስ መስጠትን መቃወም / የመስክ ተቆጣጣሪው ለኃላፊው ሁኔታውን ማሳወቅ አለበት፡፡

ሠ/ አስቸጋሪ በሆኑ ነጥቦች ላይ የቃለ መጠይቅ መልስ ለማግኘት የመስክ ተቆጣጣሪው ወደ መስክ መሄድ አለበት፡፡

ረ/ መልስ ያልተሰጠባቸው ጥያቄዎች በአንዳንድ ቦታ በተለያዩ ምክንያቶች በጣም ሊበዙ ይችላሉ/ ለምሣሌ፣ ባለይዞታውን ባለማግኘት ወይም ብዙ ባለይዞታዎች ቃለ መጠይቅ መደረጉን ሲቃወሙ / በዚህ ጊዜ የችግሩን አሳሳቢነት በመግለጽ ለኃላፊው ሁኔታውን አሳውቆ ይህንኑ አካባቢ እንዲጎበኘ ው ማድረግ የመስክ ተቆጣጣሪው ኃላፊነት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥንቃቄ የተሞላበት ምዝገባ ማካሄዱን ማረጋገጥ፣ መረጃ ሰብሳቢው መረጃውን በመስብሰብ ረገድ ተደጋጋሚ ጉብኝት በማድረግ የተቻለውን ሁሉ መሞከሩን ማረጋገጥ፣ መረጃ ሰብሳቢው በቅርብ ሆኖ መረጃውን ለመሰብሰብ የሚያደርገውን ጥረት መከታተል አስፈላጊም ሲሆን መርዳት፣ መረጃ ሰብሳቢው ከብዙ ሙከራ በኋላ መረጃ መሰብሰቡ የማይሳካለት ከሆነ የመስክ ተቆጣጣሪው እራሱ መሞከር የግብርና ጥናቱን የመስክ ሥራ የተሳካ ያደርገዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

## 5.3 <u>ባለይዞታውን በተመረጠው ቆጠራ ቦታ ማግኘት ያለመቻል</u>

የተመረጠው ባለይዞታ በቃለ መጠይቁ ጊዜ መገኘቱን ማረጋገጥና አስፈላጊ የሆኑትን መመሪያዎች ለመረጃ ሰብሳቢው መስጠት የመስክ ተቆጣጣሪው ተግባር ነው:: ለምሣሌ ፣ መንገድ መሪ ፣ አስተርጓሚ ... ወዘተ ተደርጎ የተመረጠው ባለይዞታን መረጃ ሰብሳቢው ላያገኘው ይችል ይሆናል:: ከእንደዚህ ዓይነት ያልተሳካ ተደጋጋሚ ጉብኝት በኂላ መረጃ ሰብሳቢው ጉዳዩን ለመስክ ተቆጣጣሪው ማሳወቅ እንዳለበት ተገልጿል:: በዚህ ጊዜ :-

ሀ/ የተመረጠው ባለይዞታ የትና መቼ እንደሚገኝ፣ መረጃ ሰብሳቢው በቂ መረጃ መሰብሰቡንና በመመሪያው መሰረት የሚቻለውን ሁሉ አድርጎ ባለይዞታውን ሊያገኘው አለመቻሉን ማረጋገጥ ፣ ከዚያ በኂላም ያላሰለሰ ጥረት በተጨማሪ መረጃ ሰብሳቢው እንዲያደርግ ማድረግ ፣

ለ/ መረጃ ሰብሳቢው ባለይዞታውን በመመሪያው መሠረት መምረጡንና ጉብኝቱንም በትክክል ማድረጉን ማረጋገጥ ፣

ሐ/ በሁለተኛ ደረጃ በተጠቀሰው ዘዴ ካልተሳካ ባለይዞታውን ለማግኘት የመስክ ተቆጣጣሪው እራሱ ጥረት በማድረግ ጉብኝቱ እንዲሳካ ማድረግ ፣ በመጨረሻ እንደዚህ ዓይነት ችግር በመስክ ላይ በተደጋጋሚ ከታየ የመስክ ተቆጣጣሪው ሁኔታውን ለኃላፊው ማሳወቅ ወይም የተመረጠው ቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ገበሬ ማህበር ሊቀመንበርን እርዳታ መጠየቅ:: በአንዳንድ ምክንያት በናሙና ቆጠራ ቦታ ምንም ባለይዞታ ሊገኝ ካልቻለ/በፀጥታ ምክንያት . . . ወዘተ/ ሁኔታውን ለዋናው መ/ቤት ማሳወቅ በጣም አስፈላጊ ነው::

## 5.4 <u>የተመረጠው ባለይዞታ ከተገኘ በኂላ የሚኖረው ሁኔታ</u>

ሀ/ <u>መረጃውን ሰብስቦ ማጠናቀቅ</u>፣ ባለይዞታው ከተገኘ በኂላ ቃለ መጠይቁን በማድረግ፣ማሣ በመለካት ወይም ሰብል አጨዳውን አስመልክቶ መረጃ ሰብሳቢው መረጃ የመሰብሰብ ሥራውን ያጠናቅቃል::

ለ/ <u>ተቃውሞ፣</u> አንዳንድ ጊዜ የተመረጠው ባለይዞታ ቃለ መጠይቅ መደረግ ወይም ማሳውን ማስለካት ላይፈልግ ይችላል:: ባለይዞታው ለግብርና ናሙና ጥናቱ የመተባበሩ ፍላጎት በመረጃ ሰብሳቢው አቀራረብ ላይ ይወስናል:: መረጃ ሰብሳቢው ለተመረጠው ባለይዞታ መጀመሪያ እራሱን በትህትና ማስተዋወቅ፣ የጥናቱን ዓላማ ግልጽ በሆነ መንገድ ማስረዳትና የሚሰበሰበው መረጃ

ሚስጥራዊ ሆኖ የሚቆይ መሆኑን መግለጽ አለበት:: ከዚህ በኋላ ባለይዞታው ቃለ መጠይቁን ፣ የማሳውን ልኪና የሰብል አጨዳውን የሚቃወም ከሆነ ሁኔታውን መረጃ ሰብሳቢው ለመስክ ተቆጣጣሪው ማሳወቅ አለበት:: የተመረጠው ባለይዞታ ተቃውሞ እንደ መጨረሻ ውጤት መወሰድ የለበትም:: ሰዎች ለመቃወም ብዙ ምክንያቶች ይኖሩዋቸዋል:: ከነዚህም አብዛኛዎቹ ትህትና በተሞላበትና ትክክለኛ በሆነ አቀራረብ ሊቃለሉ የሚችሉ ስለሚሆኑ በዚሁ መንገድ መቅረብ ሁኔታውን ሊያሻሽለው ይችላል:: ከተቻለ የአካባቢውን ህዝባዊ ድርጅቶች ተጠሪ እንደ የገበሬ ማህበሩ ሊቀመንበር . . . ወዘተ/ ይዞ በመሄድ የተቃወመውን ባለይዞታ በማሳመን እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ::

## 5.5 የተመረጠው ባለይዞታ እቤቱ ከሌለ

በመረጃ አሰባሰቡ ወቅት የሚፈለገው ወይም የተመረጠው ባለይዞታ እቤቱ አለመገኘ ት ብዙ ጊዜ የሚያጋጥም ችግር ነው:: በዚህ ጊዜ መረጃ ሰብሳቢው ባለይዞታውን ለማግኘት ሌላ ቀጠሮ መያዝ ይኖርበታል:: ሁኔታውን በማስታወሻው ላይ በማስፈር ባለይዞታው ቃለ መጠይቅ ያልተደረገለት ለመሆኑ ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል::

## 5.6 በተለያዩ ምክንያቶች ስላልተጠናቀቀ/ስላልተሟላ መረጃ

መረጃዎች በተለያዩ ምክንያት ላይጠናቀቁ ወይም ላይሟሉ ይችላሉ:: ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

1. በመረጃ ሰብሳቢው የአያያዝ ጉድለት አንዳንዶቹ ቅጾች ከመሀል ተነጥለው ሲጠፉ ፣
2. የተመረጠው ባለይዞታ አንዳንድ ጥያቄዎችን ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ፣
3. ቃለ መጠይቁ ከመጠናቀቁ በፊት አንዳንድ ያለመግባባት በመሀል ከተፈጠረና ቃለ መጠይቁ ከተቋረጠ ፣

ስለዚህ መረጃ ሰብሳቢው ማንኛውንም ቅጽ ይሁን መጠይቅ በሚገባ መጠናቀቁን ማረጋገጥ ሲኖርበት ያልተጠናቀቀ ካለ በተደጋጋሚ ጉብኝት በያዘው ቀጠሮ መሠረት ማጠናቀቅ ይገባዋል:: ሆኖም ተደጋጋሚ ጉብብት ማድረግ የማይቻል ከሆነ ሁኔታውን ለመስክ ተቆጣጣሪው ማሳወቅ ይኖርበታል::

በተጨማሪም የመስክ ተቆጣጣሪው በቅጾቹ ላይ አንዳንድ እርምት በሚሰጥበት ጊዜ ያልተጠናቀቁ ቅጾች እንዲጠናቀቁ ማድረግ አለበት:: የመስክ ተቆጣጣሪው

ያልተጠናቀቁ ቅጾች በሚያጋጥሙበት ጊዜ መረጃውን ከመረጃ ሰብሳቢው ማግኘት የሚቻል ከሆነ እዚያው እንዲጠናቀቅ ማድረግ ሲገባው መረጃው አስፈላጊ የሆነና ከመረጃ ሰብሳቢው የሚገኝ ካልሆነ ሌላ ቀጠሮ ከባለይዞታው ጋር ይዞ መረጃ ሰብሳቢው መረጃውን እንዲያሟላ ማድረግ አለበት፡፡

## 6. ጥናቱ ከመጠናቀቁ በፊት የሚከናወኑ ተግባራት

1. እያንዳንዱ መረጃ ሰብሳቢ የጥናቱን ሥራ እንደፈጸመ መረጃዎች ያልተሰበሰበለት ወይም በከፊል ብቻ የተሰበሰበለት በናሙና የተመረጠ ቤተሰብ ወይም ባለይዞታ እንዳይኖር ቅጾችን በጥንቃቄ እንዲመረምርና ከተሞሉት መጠይቆች ጋር እንዲገናዘብ መመሪያ መስጠትና የህንን ማድረጉን መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ ያልተሸፈነ ወይም በከፊል መረጃ የተሰበሰበለት ቤተሰብ ወይም ባለይዞታ ካለ በአስቸኳይ እንዲጠናቀቅ ማድረግና እንደዚሁም የተሞሉትን መጠይቆች አንድ በአንድ በማየት በትክክል መሞላታቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ይገባል፡፡
2. መረጃ ሰብሳቢዎች የሞሏቸው መጠይቆችም በናሙና ከተመረጡት ቤተሰቦችና ባለይዞታዎች ዝርዝር ጋር ሙሉ በሙሉ የሚገናዘቡ መሆኑን በማስተያየት በናሙና የተመረጡት ባለይዞታዎች ያልተዘለሉ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ያልተሸፈኑ ባለይዞታዎች መኖራቸው ከተረጋገጠ የሚመለከታቸው መረጃ ሰብሳቢዎች ባለይዞታው ድረስ ተመልሰው መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ማድረግ ይገባል፡፡
3. በመጨረሻም እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ከእያንዳንዱ መረጃ ሰብሰቢ የተረከባቸውንና በእጁ ያሉትን የተሞሉ ቅጾች ፣ ሌሎች ዶክሜንቶችንና ማቴሪያሎች ብዛትና ዓይነታቸው ለመረካከቢያ የተዘጋጁትን ቅጾች በመጠቀም መረካከብና ለኃላፊው/ ጽ/ቤት ተቆጣጥሮ በፊናው ማስረከብ አለበት፡፡

## 7. በመረጃ ሰብሳቢዎች ላይ ሊታዩ የሚችሉ ጉልህ ድክመቶችና መውሰድ የሚኖርባቸው እርምጃዎች

አብዛኛዎቹ መረጃ ሰብሳቢዎች በታታሪነትና በታማኝነት እንደሚሰሩ ይታመናል፡፡ ጥሩ አመራርና ቁጥጥር ከተደረገላቸው የመረጃ አሰባሰቡ ሥራ በታቀደው መሠረት በጥራትና በፍጥነት ሊጠናቀቅ ይችላል፡፡ ሆኖም ችግርን በመፍታት ፋንታ ችግር የሚፈጥሩ ፣ ሥራን የሚያድበሰብሱና በሐቅ የማይሰሩ መረጃ ሰብሳቢዎች አልፎ አልፎ ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች

የተመለከቱትና የመሳሰሉት ድክመቶች በመረጃ ሰብሳቢዎች ላይ እንዳይታዩ በጥብቅ መከታተልና መቆጣጠር የእያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ኃላፊነት ነው፡፡

1. አንዳንድ መረጃ ሰብሳቢዎች ከተሰጠው መመሪያ ውጭ ከቤት ቤት / ከይዞታ ይዞታ / በመዘዋወር ትክክለኛ መረጃዎችን በመሰብሰብ ፋንታ የሀሰት መረጃዎችን በመጠይቁ ላይ ሊሞሉ ይችላሉ፡፡ ይህውም በሰዋራ ወይም በአስቸጋሪ ቦታ ውስጥ በመሆናቸው ቤቶችን የመዝለልና በትክክል ያለመሸፈን ድክመት ሊታይ ይችላል፡፡ እዚህም ላይ ስላልታወቀና ስለፈጠራ ቤተሰቦች አባላት የፈጠራ መረጃዎችን የመሰብሰብ ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በመሆኑም ትክክል ያልሆነ ስራ ሲሰራ የተገኘን መረጃ ሰብሳቢ ተቆጣጣሪው በጥብቅ መቆጣጠርና ለኃላፊው ማሳወቅ አለበት፡፡
2. አንዳንድ መረጃ ሰብሳቢዎች ለጥናቱ ባላቸው ኃላፊነት የተነሳ በድፍረት ገንዘብ ወይም የመሳሰሉ ጥቅሞችን በመጠየቅና በማስገደድ ከባለይዞታዎች ለማግኘት ይሞክሩ ይሆናል፡፡ በእንደዚህ አይነት የተጠረጠረና የተረጋገጠበት መረጃ ሰብሳቢ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድበት ለኃላፊው ማሳወቅ አለበት፡፡
3. አንዳንድ መረጃ ሰብሳቢዎች ከጥናቱ ስራቸው በተጨማሪ ዕቃዎችን ከከተማ ወደ ገጠር በመውሰድ በመሸጥና በመለወጥ ተግባር ላይና በመሳሰሉት ተግባሮች ላይ ይሰማሩ ይሆናል፡፡ ይህም የጥናቱን ስራ የሚያደናቅፍና የሚያጓትት ስለሆነ እንዲህ የሚያደርጉትን መረጃ ሰብሳቢዎች አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለኃላፊው ማሳወቅ አለበት፡፡
4. አንዳንድ መረጃ ሰብሳቢዎች በጥናቱ በሚሳተፉበት ወቅት መልካም ስነ ምግባር የጎደለው ባህርይ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ይህም ፈጽሞ ሊሆን የማይገባው ሁኔታ ስለሆነ እንደዚህ ዓይነት ባህርይ ያሳየውን መረጃ ሰብሳቢ መምከርና ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

እነዚህና የመሳሰሉትን ድክመቶች በእንጭጩ ለመቅጨትና ለማስተካከል የሚቻለው የጥናቱ ሥራ ከተጀመረበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ሳይታክቱ ትጋት የተሞላበት ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ብቻ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ድርሻውን እንዲወጣ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡

## የ1999 ዓ/ም የሰብል ትንበያ ናሙና ጥናት የኤዲቲንግ አጭር መመሪያ

### 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ በ1998 ዓ/ም በመስከረም ወር የሰብል ትንበያ ጥናት ያካሄዳል::

በዚህም ጥናት በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የሰብል ሁኔታ ግምገማና የእርሻ ስራን ሁኔታ የሚያመለክቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ይሰበሰባሉ:: እነዚህንም የሚሰበሰቡ መረጃዎች ወደ ባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት በማምጣት የመረጃ ማቀነባበር ስራና የሪፖርት ዝግጅት ስራ ይከናወናል:: ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ወደ መስሪያ ቤቱ ከመምጣታቸው በፊት በመስክና በቢሮ መጠነኛ የኤዲቲንግ ስራ በመስክ ተቆጣጣሪዎች አማካኝነት ይደረጋል::

ስለዚህ በዚሁ ስራ የሚሳተፉ የመስክ ስራ ተቆጣጣሪዎች አንድ ዓይነት የአሰራር መመሪያ እንዲከተሉ ይህ የኤዲትንግ መመሪያ ተዘጋጅቷል:: መረጃ የተሞላባቸው የሰብል ሁኔታ ግምገማ ቅጾች የኤዲትንግ መመሪያ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል::

### 2. ትርጉም

ኤዲቲንግ ማለት በተሰጠው መመሪያ መሠረት ለተሰበሰበው መረጃ አስፈላጊ እርምት ማድረግ ነው:: በሰብል ትንበያ ጥናት የተሰበሰቡትን መረጃዎችን ኤዲት ማድረግ የመረጃውን አሰባሰብ ጥራት ለመገምገምና እንዲሁም ስህተቶችን፣ የሚቃረኑ መረጃዎችንና፣ ሳይሞሉ የቀሩ መረጃዎችን አሰባሰብ በማረም የመረጃውን ጥራት ለማሻሻል ይረዳል::

የመስክ ስራ ተቆጣጣሪው ይህንን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት መረጃው ለጥናቱ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት መሞላቱን ማረጋገጥ አለበት::

1. <u>የቅጽ ሲ.ት.ጥ 99/3ሀ የሰብል ሁኔታ ግምገማ</u>

<u>ክፍል 1</u> <u>የአካባቢ መለያ</u>

<u>ዓምድ 1-5</u> ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ የገ/ማህበር/ሠፈራ ጣቢያ ስምና የቆጠራ ቦታ/መንደር ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 99/1 ከዓምድ 1-5 ተወስዶ መሞላቱን ማረጋገጥና በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤቱ ከተሰጠው ኮድ መመሪያ ትክክለኛውን ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ::

<u>ዓምድ 6</u> <u>**የሰብል ስም:-**</u> በዚህ ዓምድ በመረጃ ሰብሳቢው መመሪያ በገጽ 43 የተገለጹት የሰብል ዓይነቶች ከቅጽ ግ.ና.ጥ 99/2ሀ በትክክል ከተመረጡት 25 የግብርና ቤተሰቦች ለሚገኙ ባለይዞታዎች በሙሉ መተላለፉንና ትክክለኛው ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ::

<u>ክፍል 2</u> የሰብል ሁኔታ ግምገማ/በመኸር ወቅት/

<u>ዓምድ 1</u> <u>ተራ ቁጥር:-</u> በዚህ ዓምድ ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር ተሞልቷል::

<u>ዓምድ 2</u> <u>**የባለይዞታው ስም**</u>:- በክፍል 1 ዓምድ 6 የተመዘገበው ሰብል በማሳዎቹ ላይ ያለው ባለይዞታ ስም ከቅጽ ግ.ና.ጥ 99/1 ክፍል 2 ዓምድ 5 መተላለፉን ማረጋገጥ::

<u>ዓምድ 3</u> <u>**የቤተሰብ መለያ ቁጥር:-**</u> ከላይ በዓምድ 2 የተመዘገበው ባለይዞታ የቤተሰብ መለያ ቁጥር በትክክል ከቅጽ ግ.ና.ጥ 99/1 ክፍል 2 ዓምድ 1 መተላለፉን ማረጋገጥ::

<u>ዓምድ 4</u> <u>**የባለይዞታው መለያ ቁጥር**</u> :- ከላይ በዓምድ 2 የተመዘገበው ባለይዞታ በዚህ ዓምድ የተሞላለት የባለይዞታ መለያ ቁጥር ከቅጽ ግ.ና.ጥ 99/1 ክፍል 2 ዓምድ 4 መተላለፉን ማረጋገጥ::

<u>ዓምድ 5</u> <u>**የማሳዎች ብዛት:**</u>- ከላይ በዓምድ 2 የተመዘገበው ባለይዞታ ስም ትክክል መሆኑ የተረጋገጠለት ባለይዞታ በክፍል 1 ዓምድ 6 በተመዘገበው ሰብል የተያዙ ማሣዎች ብዛት በዚህ ዓምድ መሞላቱንና ትክክል መሆኑን ከቅጽ 98/2ሀ ጋር በማመሳከር ማረጋገጥ:: ይህ ዓምድ በምንም ዓይነት በሠረዝ አይታለፍም:: በተጨማሪም አንድ ማሳ በድብልቅ ሰብሎች የተያዘ ከሆነ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊቆጠር እንደሚችል ማስታወስ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 6</u> የሰብል ምርት ከአለፈው ዓመት ጋር በማነጻጸር ባለይዞታው ይጨምራል ካለ ኮድ «1»፣ ለውጥ የለም/እኩል ነው ካለ ኮድ «2» ፣ይቀንሳል ካለ ኮድ «3» በዚህ ዓምድ ተገልጾ ለኮድ መጻፊያ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ከሶስቱ

አማራጮች ተስማሚው ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ:: በዚህ ዓምድ ኮድ «2» ከተሞላ ከዓምድ 7-10 ባዶ መተዋቸውን ማረጋገጥ ያሻል::

ዓምድ 7 በዓምድ 6 ኮድ «1» ከተሞላ በዚህ ዓምድ የሚጨምረው ምርት መጠን በመቶኛ መሞላቱን ማረጋገጥ::

ዓምድ 8 በዓምድ 6 ኮድ «1» ከተሞላና በዓምድ 7 የሚጨምረው መጠን በመቶኛ ከተገለጸ በዚህ ዓምድ ለምርታማነት መጨመር አንድ ዋንኛ ምክንያት መሞላቱን ማረጋገጥ :: ከአንድ ምክንያት በላይ ከተገለጸ በተቀራረበ አካባቢ ለሚገኙ ባለይዞታዎቸ ከተሞሉ መረጃዎች ጋር በማመሳከር ተጨባጭ የሆነ አንድ ምክንያት መያዝ ያስፈልጋል:: ለተመዘገበው የምርታማነት መጨመር አንድ ዋና ምክንያት በገጽ ------ ውስጥ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ኮድ ተስማሚውን በመምረጥ በተሰጠው ክፍት ቦታ መሙላት ያስፈልጋል::

ዓምድ 9 በዓምድ 6 ኮድ «3» ከተሞላ በዚህ ዓምድ የሚቀንሰው ምርት መጠን በመቶኛ መሞላቱን ማረጋገጥ በተጨማሪም ምርት ከ100 ፐርሰንት በላይ/ማለትም 150 ፣ 200 ፣ 300 . . . ወዘተ/ሊቀንስ ስለማይችል በዚህ ዓምድ ከ100 ፐርሰንት በላይ ምርት መቀነሱ ተመዝግቦ ከተገኘ የተመዘገበውን በመሠረዝ በምትኩ 100 መመዝገብ ይኖርበታል::

ዓምድ10 በዓምድ 8 የሚቀንሰው ምርት መጠን በመቶኛ መሞላቱን እንደተረጋገጠ በዚህ ዓምድ ለምርታማነት መቀነስ አንድ ዋና ምክንያት መመዝገቡን ማረጋገጥና ከአንድ በላይ ምክንያት የተገለጸ እንደሆነ በተቀራረበ አካባቢ ለሚገኙ ባለይዞታዎች ከተሞሉ መረጃዎች ጋር በማመሳከር ተጨባጭ የሆነ አንድ ምክንያት መያዝ ያስፈልጋል:: ለተመዘገበው የምርታማነት መቀነስ አንድ ዋና ምክንያት በሠንጠረዥ ---- ውስጥ ከተዘረዘሩት የምርታማነት መቀነስ ዋና ዋና ምክንያቶች ኮድ ተስማሚውን በመምረጥ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ መሙላጥ::

ዓምድ11 በዓምድ 7 የሚጨምረው ምርት መጠን በመቶኛ መሞላቱ እንደተረጋገጠ በዚህ ዓምድ ውስጥ በዓምድ 7 የተሞላው መጠን ላይ 100 በመደመር የተገኘው ውጤት በትክክል መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ሆኖም በዓምድ 6 ኮድ «2» ከተሞላ ወይም ከዓምድ 7-10

ባዶ ከተተወ/በሠረዝ ከታለፈ በዓምድ 11፣ 100 መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዓምድ 9 የምርታማነት መቀነስ በመቶኛ መሞላቱ ከተረጋገጠ በዓምድ 9 የተመዘገበውን ከ100 በመቀነስ የሚገኘው ውጤት በዓምድ 11 በትክክል መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም አንድ ባለይዞታን ብቻ በተመለከተ ከዓምድ 6-10 እርስ በርሱ የሚቃረን ነገር ተመዝግቦ ከተገኘ ለመረጃ ሰብሳቢው በማስረዳት መረጃውን እንደገና በመመሪያው መሠረት ማረም አስፈላጊ ነው፡፡

## ቅጽ ግ.ና.ጥ. 99/6ሀ የምግብ ዋስትና መጠይቅ

ይህ ቅጽ በመደበኛ ቆጠራ ቦታዎች በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ለሚገኙ የቤተሰብ ኃላፊዎች በሙሉ  የምግብ ዋስትና መረጃ የሚሞላበት ነው፡፡ ክፍል አንድ የአከባቢ መለያ የሚሞላበት ሲሆን ከቅጽ 99/1 መወራረስ ያለባቸው መረጃዎች በትክክል መወራረሳቸውንና ተጠይቀው የሚሞሉ ዓምዶች ደግሞ በሚገባ ተጠይቀው መሞላታቸውን ተቆጣጣሪው ማረጋገጥ አለበት፡፡

ክፍል ሁለት የተመረጠው የቤተሰብ ኃላፊ በ1999 ዓ.ም. የሰብል ምርት ዘመን የነበረው የምግብ ዋስትና ሁኔታ ተጠይቆ የሚሞላበት ነው፡፡ በዚህም ክፍል የሚሞላው መረጃ ጥራቱን የጠበቀ እና መመሪያውን የተከተለ መሆኑን እንዲሁም ኮዶች በትክክል መሞላታቸውን ተቆጣጣሪው በሚገባ ማረጋገጥ አለበት፡፡

## የቅጽ ግ.ና.ጥ.99/6ለ የሠፈራ ጣቢያ የምግብ ዋስትና መጠይቅ

ይህ ቅጽ በሠፈራ ቦታው በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ ለሚገኙ የቤተሰብ ኃላፊዎች በሙሉ የምግብ ዋስትና መረጃ የሚሞላበት ነው፡፡ ሠፈራ ጣቢያን የሚመለከቱ የተወሰኑ ጥያቄዎች ከመጨመራቸው በስተቀር የቅጹ ይዘት ከሞላ ጎደል ከቅጽ  ግ.ና.ጥ. 99/6ሀ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ክፍል አንድ የአከባቢ መለያ የሚሞላበት ሲሆን ከቅጽ 99/1 መወራረስ ያለባቸው መረጃዎች በትክክል መወራረሳቸውንና ተጠይቀው የሚሞሉ ዓምዶች ደግሞ በሚገባ ተጠይቀው መሞላታቸውን ተቆጣጣሪው ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ክፍል ሁለት የተመረጠው የቤተሰብ ኃላፊ በ1999 ዓ.ም. የሰብል ምርት ዘመን የነበረው የምግብ ዋስትና ሁኔታ ተጠይቆ የሚሞላበት ሲሆን በዚህም ክፍል የሚሞላው መረጃ ጥራቱን የጠበቀ እና መመሪያውን የተከተለ መሆኑን እንዲሁም ኮዶች በትክክል መሞላታቸውን ተቆጣጣሪው በሚገባ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

| ተ.ቁ | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | መግቢያ | 1 |
| | 1.1. ትንበያ የእርሻ ሰብል ናሙና ጥናት ዓላማዎች | 1 |
| | 1.2. የሰብል ምርት ትንበያ ናሙና የሚያስገኛቸው ጥቅሞች | 2 |
| | 1.3. የግብርና ናሙና ጥናት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች | 2 |
| 2 | የግብርና ናሙና ጥናት የተቆጣጣሪዎች አጠቃላይ መመሪያ | 3 |
| | 2.1. የተቆጣጣሪ ሚና | 3 |
| | 2.2. ሥልጠና | 4 |
| 3 | የመስክ ተቆጣጣሪ መሠረታዊ ተግባሮች | 5 |
| | 3.1. የሥራ አፈጻጸሞችን መቆጣጠርና አስተዳደራዊ ሥራዎችን ማከናወን | 5 |
| | 3.2. የተቆጣጣሪን ቴክኒካዊ የመስክ ቁጥጥር ማድረግ በሚመለከት የሚከናወኑ ተግባራት | 6 |
| 4 | መጠይቆችን ስለመመርመር | 7 |
| | 4.1. አጠቃላይ መመሪያ | 7 |
| | 4.2. የመጠይቆችን አሞላል ስለመመርመር ዝርዝር መመሪያ | 7 |
| 5 | መልስ ያልተሰጠባቸውንና ተመሳሳይ ሁኔታዎችን በሚመለከት | |
| | 5.1. «መልስ ያልተሰጠባቸው» ማለት ምን ማለት ነው? | 14 |
| | 5.2. መልስ ያልተሰጠበቸውን በሚመለከት አጠቃላይ መመሪያ | 14 |
| | 5.3. ባለይዞታውን በተመረጠው ቆጠራ ቦታ ማግኘት ያለመቻል | 15 |
| | 5.4. የተመረጠው ባለይዞታ ከተገኘ በኂላ የሚኖረው ሁኔታ | 16 |
| | 5.5. የተመረጠው ባለይዞታ እቤቱ ከሌለ | 17 |
| | 5.6. በተለያዩ ምክንያቶች ስላልተጠናቀቀ/ስላልተሟላ መረጃ | 17 |
| 6 | ጥናቱ ከመጠናቀቁ በፊት የሚከናወኑ ተግባራት | 18 |
| 7 | በመረጃ ሰብሳቢዎች ላይ ሊታዩ የሚችሉ ጉልህ ድክመቶችና መወሰድ የሚኖርባቸው እርምጃዎች | 18 |
| 8 | 1997 ዓ.ም የሰብል ትንበያ ናሙና ጥናት የኤዲቲንግ አጭር መመሪያ | 20 |
| 9 | 1997 ዓ.ም ግብርና ናሙና ጥናት መረጃ የተሞላባቸው ቅጾች ወደ ዋናው መ/ቤት መመለሻ ወቅት | 28 |